MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

## የተራዘመ የትምህርት ዓመት አገልግሎቶች

# ESY

2017-2018

የሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ልዩ የትምህርት አገልግሎቶችን ለሚቀበሉ ተገቢ(ብቁ) ተማሪዎች የተራዘመ የትምህርት ዓመት (ESY) አገልግሎቶችን ይሰጣል።
እነዚህ አገልግሎቶች በሰመር/summer ወቅት/በበጋ የሚሰጡ ነፃ እና አግባብነት ያለው የህዝባዊ ትምህርት (FAPE) አካል ናቸው ።
ይህ መፅሄት የESY አገልግሎቶችንና የብቃት መስፈርቶችን እንድትገነዘቡ ለማገዝ የተዘጋጀ ነው።

Montgomery County Public Schools

የልዩ ትምህርት ጽ/ቤት
Office of Special Education

## የተራዘመ የትምህርት ዓመት አገልግሎቶች ምንድን ናቸው?

የተራዘመ የትምህርት ዓመት (ESY) በአንድ ተማሪ ልዩ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ውስጥ የተካተቱ ግቦችና ዓላማዎችን ለመድረስ የተተለሙ ከመደበኛ የትምህርት ዓመት ባሻገር የልዩ አገልግሎቶች ልዩ ተቀጥያ ናቸው። ESY የትምህርት ዓመት ማርዘሚያ ማለት አይደለም። አውቶማቲክ የበጋ ወቅት/summer የትም/ቤት ምደባ ለማዳበርም አይደለም፤ ወይም ደግሞ እያንዳንዱ ስንክልና ያለው ተማሪ ESY ያስፈልገዋል ማለትም አይደለም። በትክክለኛው ESY ማለት ስንክልና ላላቸው ለጥቂት ተማሪዎች ብቻ ተገቢ ሊሆን ይችላል። የሆነ ሆኖ፣ የIEP ቡድን በአመታዊ የግምገማ ስብሰባ ላይ ማንኛውንም ልዩ የትምህርት አገልግሎቶች የሚቀበል/የሚሳተፍ ተማሪ ለESY ብቃት/ተገቢነቱን እንዲያገናዝብ ህጋዊ ኃላፊነት አለበት። በተማሪው ፍላጎቶች መሰረት፣ የESY አገልግሎቶች በአይነት፣ በብዛት/ጥንካሬ፣ በቦታ፣ የተያያዙ አገልግሎቶችን በማካተት፣ እና በጊዜ ብዛት ሊለያዩ ይችላሉ።

## የESY አገልግሎቶች ሊያስፈልጋቸው የሚችል ተማሪዎች ለምሳሌ፡-

- ★ የምግብ ምርጫው(ዋ)ን የመግለጽ ችሎታ ፍንጭ ያገኘ/ች የአእምሯዊ ስንክልና ያለው/ያላት የ8 ተማሪ፣ ያለ ESY አገልግሎቶች፣ ይህን ፍንጭ/ችሎታ የሚያጣ/የምታጣ ከሆነ፣
- ★ የአእምሮ ዝግመት ተጠቂ የሆነ/ች ተማሪ ራስን የማቁሰል/የመጉዳት ተደጋጋሚ ባህርይ/ሁኔታን ለመቀነስ በታለመለት ዓላማ በቅርቡ ማህበራዊ/የመግባባት ጠባይ ለውጥ የታየበ(ባ)ት እና የ ESY አገልግሎት ካላገኘ/ች በስተቀር ራስን የመጉዳት ጠባይ ቀድሞ ወደነበረበት ደረጃ የመመለስ አዝማሚያ የሚታይበ(ባ)ት፣
- ★ የእድገት ዘገምተኝነት ያለው/ያላት የ 4-ዓመት-እድሜ ተማሪ በት/ቤት የጊዜ ሠሌዳ ለመፀዳዳት በቃል ሲነገረው/ሲነገራት ማስታወስ የሚችል/የምትችል እና ሰመር/Summer ላይ ወደ ነበረበት ሁኔታ የመመለስ እድል ስለሚኖረው/ስለሚኖራት ፎል / fall ላይ ወደ ሙሉ ቀን የትምህርት ፕሮግራም ሲመለስ/ስትመለስ እንደገና ማሰልጠን እጅግ አስፈላጊ የሚሆን ከሆነ፣
- ★ የ10 አመት ተማሪ የአእምሮ ስናክልናና የመንቀሳቀስ ችግር /ሽባ የመሆን ችግር/ (cerebral palsy)ያለው/ያላት፡- የመነጋገርያ መሳርያ (augmentative communication device) ካለፈው ፎል ጀምሮ ለመጠቀም ሲማር/ስትማር የነበረ/ች። ከባለ ስድስት እርምጃ ሂደት የመጀመሪያዎቹን ሁለቱን እርምጃዎች ብቻውን/ብቻዋን፡- ለማከናወን ተማሪውን/ተማሪዋን፡- ስድስት ወራት ወስዶበ/ባታል። በዚህ ወሳኝ የችሎታ ፍንጭ ማግኘት ምክንያት እና አዲሱ ትምህርት ስለሚጠይቀው ጊዜ፣ ESY አስፈላጊ መሆኑ አስተያየት ይሰጣል።
- ★ በስፕሪንግ /ፀደይ/ ማለቂያ አካባቢ ላይ፣ አንድ/አንዷት ልዩ የመማር ስንክልና ያለው/ያላት ልጅ በምልክት/ምልክቶችን በማንባብ ስኬታማ ሆኗል/ሆናለች። ወደ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት (ሚድል ስኩል) በሚሸጋገሩበት ጊዜ የጀመሩትን ስልጠና/skills/ ESY ማስቀጠል ይኖርበታል።

## የESY ውሳኔዎች እንዴት ነው የሚከናወኑት?

እንደተለመደው፣ ለተከታዩ ዓመት የESY አገልግሎቶች ተገቢነት/ብቃት ያላቸው የሚወሰኑት IEPን ለመቅረጽ በሚካሄደው በዓመታዊው የIEP ቡድን የግምገማ ስብሰባ ወቅት ነው። ስንክልና ያለባቸው ተማሪ ወላጆች/አሳዳጊዎች ከት/ቤት ሰራተኛ ጋር በመሆን ጠቅላላውን የ IEP ክፍሎችን በማጎልበትና የESY አገልግሎቶችን በመስጠት እኩል ተሳታፊዎች ናቸው። የIEP ቡድን አባሎች የሚከተሉትን ያካትታል፡-

፡- የተማሪው/ዋ ወላጆች/አሳዳጊዎች

፡- ተማሪው/ዋ (አግባብነት ካለው)

፡- የMCPS ተወካይ

፡- የአጠቃላይ ትምህርት መምህር

፡- የልዩ ትምህርት መምህር

፡- የመማርያ ክፍል መምህር፣ እና

፡- ወላጆች/አሳዳጊዎች ወይም የት/ቤት ሰራተኛ አባላት ለሂደቱ አስተዋፅኦ ማድረግ ይችላሉ ብለው የሚሰማቸው ሌሎች የሚከተሉትን የመሳሰሉ፡-

፡- የንግግር ፓቶሎጂስት/speech pathologist

፡- ከስራው ጋር ተያያዥነት ያለው/ያላት ሀኪም/occupational therapist

፡- አካላዊ ሀኪም/therapist፣ እና

፡- የዕይታ ወይም የእንቅስቃሴ መምህር

፡- ከአመታዊው ግምገማ ስብሰባ ይልቅ ይበልጥ ተገቢ ሆኖ ከተገኘ ስለ ESY የሚደረጉ ውሳኔዎች በወቅታዊ ግምገማ ስብሰባዎችም መከናወን ይችላሉ።

## የESY ብቃት እንዴት ነው የሚወሰነው?

1. የIEP ቡድን አባላት ለፕሮግራሙ አገልግሎቶች ብቃት ለመወሰን እነዚህን ታሳቢዎች ግምት ውስጥ ያስገባሉ። ወደነበረበት መመለስ (መቀልበስ) (Regression/Recoupment)

   የIEP ቡድን፣ በትምህርት የእረፍት ጊዜ ምክንያት የESY አገልግሎቶች ከተቋረጡ ወሳኝ በሆኑ የህይወት አድን ክህሎት ከፍተኛ የመቀልበስ ሁኔታ ሊያጋጥም ይችል እንደሆነና የጠፉ ችሎታዎችን አግባብ ባለው ጊዜ ውስጥ ለመመለስ ይቻል/አይቻል እንደሆነ ይወስናል።

### የግስጋሴ መጠን

የIEP ቡድን በተማሪው/ዋ ላይ የታየው ወሳኝ የሆነ ህይወት የመደገፍ የIEP ዓላማ የማሳካት ርምጃ/ለውጦችን በመገምገም ያለ ESY አገልግሎቶች፣ ተማሪው/ዋ ወደነዚህ ያሳየ/ችው/ የማሻሻል እርምጃ በእነርሱ ፕሮግራሞች በመደበኛው የትምህርት ዓመት ሌሎች የትምህርት ጥቅሞችን እንዳያገኝ/እንዳታገኝ የሚከለክል እንደሆነ ይገመግማል።

### ብቅ ያሉ/የተስተዋሉ ችሎታዎች/ጥሰው የሚወጡ እድሎች

የIEP ቡድን በወሳኝ የህይወት ክሂሎቶች ኢላማ ያደረጉ ሁሉንም የIEP ግቦችና ዓላማዎች ማናቸውም ከነዚያ ክሂሎቶች ጥሶ የመውጣት ደረጃ መድረሳቸውን ይገመግማል። በስልጠና የተገኙ ህይወትን ለመርዳት ወሳኝ የሆኑ ክህሎቶች እዚህ ደረጃ ላይ ደርሰው እያለ፣ በትህርት ቤት ለእረፍት መዘጋት ምክንያት የትምህርቱ መቋረጥ ተማሪው/ዋን/ ያለ IEP ድጋፍ በመደበኛው የትምህርት ዓመት ከትምህርት ፕሮግራማቸው ጥቅሞችን እንዳያገኝ/እንዳታገኝ ያደርግ እንደሆነ ቡድኑ ለመወሰን ይችላል።

### ጣልቃ-ገብ ስነምግባር

በ IEP ለማሻሻል የተቀመጡ ግቦች የሆነ አመል፣ ልማድ፣ ጠብ መጫር፣መነጫነጭ፣ ራስን የመጉዳት/መቧጨር ባህርይ(ዮች) ተማሪው/ዋን/ ባለፈው የትምህርት ዓመት ከESY አገልግሎት ውጭ ከትምህርት ፕሮግራማቸው ተጠቃሚ እንዳይሆን/እንዳትሆን አግዶት/አግዷት ከሆነ ወይም የሚያስቸግረውን/የሚያስቸግራትን ባህርይ ያማከለ ጣልቃ መግባት ተማሪው/ዋን/ ከሚያገኘው/ከምታገኘው ትምህርታዊ ፕሮግራም ለሚቀጥለው ዓመት የሚያግደው/የሚያግዳት እንደሆነ የIEP ቡድን ይወስናል።

### የስንክልናው አፈጣጠር እና/ወይም ክብደት

ያለ ESY አገልግልግሎቶች፣ የተማሪው/የተማሪዋ ስንክልና ሁኔታ፥ ተማሪው/ተማሪዋ በመደበኛ የትምህርት ዓመት ከትምህርት ፕሮግራም አንዳንድ ጥቅሞችን ለማግኘት እንደማይችል የሚከለክል ከሆነ የIEP ቡድን ይወስናል። ወሳኝ የህይወት ደጋፊ ክህሎት ማለት ማንኛውም የስነ-ምግባር፣ አካዴሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ወይም በIEP ለተማሪው አጠቃላይ የትምህርት ግስጋሴ ወሳኝ ነው ብሎ የወሰነው ሌላ ችሎታ ነው።

### ልዩ ሁኔታዎች

የ IEP ቡድን፣ የተማሪውን/የተማሪዋን፥ ወላጆች/አሳዳጊዎች ጨምሮ፣ ያለ ESY አገልግሎት፣ በመደበኛው የትምህት ዓመት ተማሪውን/ተማሪዋን፥ ከትምህርት ፕሮግራማቸው የሚያገኙትን ጠቀሜታ ሊከለክል የሚችል ማናቸውም ልዩ ሁኔታዎች ይኖሩ እንደሆነ ለመወሰን ይችላሉ። የልዩ ሁኔታዎች ምሳሌዎች፡- በልዩ ምክንያቶች ወደ ትም/ቤት ዘግይተው የገቡ፣ በህመም ምክንያት ከመጠን በላይ በቀሪነት የተመዘገቡ፣ እና በጣም በተገደበ ስርዓት/ሴቲንግ የመመደብ ሁኔታን ያካትታል።

II. ከላይ የተዘረዘሩትን እውነታዎች በማስመልከት፣ ተማሪው IEP እና የመሻሻል እርምጃን በሚመለከት ተማሪው/ዋ ለማግኘት የሚችለውን/የምትችለውን የእነርሱ የትምህርት ፕሮግራም በመደበኛው የትምህርት ዓመት ESY ቢቋረጥ በእጅጉ ለአደጋ የሚያጋልጥ መሆን አለመሆኑን የIEP ቡድን ይወስናል። የESY አገልግሎቶች የሚያስፈልጉት አካለ ስንክልና ያላቸው ግለሰቦች የትምህርት ደንብ/Individuals with Disabilities Education Act (IDEA) መሠረት ይህ የማገርሸት/ወደ ነበረበት የመመለስ ሁኔታ፣ ትርጉም ያለው የመሻሻል ሁኔታን የሚያሰናክል ከሆነ ብቻ እና ት/ቤት ሲጀመር ተሻሽሎ ወደነበረበት በአጥጋቢ ሁኔታ መመለስ የሚያዳግት ሲሆን ነው። ይህ ከሆነ፣ ነፃ ተገቢ ህዝባዊ ትምህርት ለማግኘት ተማሪው/ዋ የESY አገልግሎቶች አቅርቦት ያስፈልገዋል/ያስፈልጋታል።

## የESY አገልግሎቶች እንዴት ይወሰናሉ?

ተማሪው/ዋ የESYን አገልግሎቶች ለመቀበል ተፈላጊዎቹን መስፈርቶች ያሟላል/ታሟላለች ብሎ የIEP ቡድን ከወሰነ፣ በESY ወቅት መሟላት ያለባቸውን ግቦችንና አገልግሎቶችን ይለያሉ። የሚከተለው መረጃ/ኢንፎርሜሽን በወቅታዊው IEP ተካቷል።

- ★ የESY አገልግሎቶችን የሚያስፈልጉ የተወሰኑ ግቦችና ዓላማዎች።
- ★ የESY IEP ዓላማዎችን ለማሳካት የሚያስፈልጉ ዓይነት(ቶች)፣ መጠን/ብዛት(ቶች)፣ የሚወስደው ያክል ጊዜ፣ እና ትራንስፖርትን ጨምሮ ልዩ ትምህርትና የተያያዘ(ዙ) አገልግሎቶች።
- ★ የESY IEP ግቦችን ለመድረስና የESY አገልግሎቶችን ለመስጠት መለስተኛ/መጠነኛ ማእቀብ የሚደረግበት ሁኔታ፡-
- ★ ስንክልና ከሌላቸው እኩያዎቹ/እኩያዎቿ ጋር፣ ተማሪው/ተማሪዋ፣ የሚሳተፍበት/የምትሳተፍበት የጊዜ ብዛት/መጠን።

በተማሪው/በተማሪዋ ፍላጎቶች በመመስረት የESY አገልግሎቶች በአይነት፣ በክብደት፣ በቦታ፣ በተያያዙ አገልግሎቶች መጨመር፣ እና በጊዜ መጠን ይለያያሉ። የESY አገልግሎቶች አጠቃላይ ትምህርት በሚሰጥባቸው ትም/ቤቶች፣ በልዩ ትም/ቤቶች፣ በማህበረሰብ፣ እና መኖሪያ ቤትን በሚያካትቱ በተለያዩ ሰፍራዎች ሊቀርቡ ይችላሉ። የIEP ቡድን ከሁሉም ይበልጥ ተገቢዎቹን የESY አገልግሎቶች እና ቦታ ለእያንዳንዱ ተማሪ ይወስናል።

## ወላጆች/አሳዳጊዎች ከIEP ቡድን ውሳኔ ጋር ካልተስማሙስ?

ወላጆች/አሳዳጊዎች በIEP ቡድን አባልነታቸው ዋጋ ይሰጣቸዋል፣ እናም ESY በልጃቸው/ተማሪያቸው ትምህርት ጉዳይ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ሙሉ በሙሉ ይሳተፋሉ። በIEP ስብሰባ ወቅት፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች ስለ IEP እና ስለ ESY ኢንፎርሜሽን/መረጃዎችን ያገኛሉ። የESY ውሳኔ አጭር የፅሁፍ መግለጫ በተጨማሪ ይቀበላሉ። ወላጆች/አሳዳጊዎች በIEP ቡድን ውሳኔ ካልተስማሙ፣ የአስተዳደራዊ ይግባኝ እንዲታይ፣ ለግልግል፣ ወይም በ301-517-5864 ለResolution and Compliance Unit በመደወል የልዩ ትምህርት ህጋዊ ችሎት መጠየቅ ይችላሉ። የአስተዳደራዊ ይግባኝ ውሳኔ ሃሳቦች በ20 ቀናት ውስጥ ይነገራሉ። አስፈላጊ ከሆነ ደግሞ፣ የፅሁፍ ጥያቄ በቀረበ በ20 ቀናት ውስጥ ሽምግልና ይመደባል። የህጋዊ ችሎት የጊዜ ሰንጠረዥ እንደሚከተለው ነው፡-

- ★ የESY ተገቢነት ያላቸውን ለመመልመል ስብሰባ ከኤፕሪል 14 በፊት ቀነ ቀጠሮ የተያዘለት ከሆነ፣ የESY ህጋዊነት ሂደት ችሎት ቀጠሮ የሚያዘው ውሳኔው የችሎት አቤቱታ በቀረበበት በ45 ቀናት ውስጥ እንደሚደረስ በማረጋገጥ ነው።
- ★ ለESY ተገቢነት ያላቸውን ለመመልመል የሚደረገው ስብሰባ በኤፕሪል 14 እና በሜይ 19 መካከል ቀነ ቀጠሮ የተያዘለት ከሆነ፣ ከሜይ 19 በፊት የተጠየቁ የESY ህጋዊ ችሎቶች በወቅታዊ መንገድ የችሎት ውሳኔ እስከ ጁን 15 ድረስ ወይም የችሎት አቤቱታ በቀረበበት በ45 ቀናት ውስጥ፣ ወይም ከማናቸውም በሚቀድመው ጊዜ እንደሚደርስ በማረጋገጥ ነው።
- ★ የESY ተገቢ የሆኑትን ለመመልመል ስብሰባ በኤፕሪል 14 እና በሜይ 19 መካከል ቀነ ቀጠሮ የተያዘለት ከሆነ፣ ከሜይ 19 በኋላ የተጠየቁ የESY ህጋዊነት ችሎቶች በወቅታዊ መንገድ የችሎት ውሳኔ አቤቱታ በቀረበበት በ20 ቀናት ውስጥ እንደሚደርስ በማረጋገጥ ነው።
- ★ ለESY ተገቢ የሆኑትን የመመልመል ስብሰባ ከሜይ 19 በኋላ ቀነ ቀጠሮ የተያዘለት ከሆነ፣ የESY ህጋዊነት ችሎቶች በወቅታዊ መንገድ የችሎት ውሳኔ አቤቱታ በቀረበበት በ20 ቀናት ውስጥ እንደሚደርስ በማረጋገጥ ነው።

## የሚቀጥለው ወላጆችን/ሞግዚቶችን፥ የልጃቸውን/የተማሪውን፥ ለ ESY ብቃት ለመገምገም በሚደረግ ዓመታዊ ስብሰባ ወቅት የሚረዳቸው መመሪያ ነው። ጥያቄዎች፡-

ተለይቶ የታወቀ ህይወት የመደገፍ ክህሎት ESY አገልግሎት ባይሰጥ ተማሪው/ተማሪዋ በመደበኛው የትምህርት ዓመት ከትምህርታቸው ፕሮግራም ለማግኘት የሚችለውን/የምትችለውን አንዳንድ ጥቅም በሚጎዳ ደረጃ ሊያገረሽበት/ሊያገረሽባት ይችላል?

☐ አዎ ☐ አይደለም

## ተከታይ ጥያቄዎች

በህይወት አድን ዓላማ የተገኘው ውስን ክህሎት መሻሻል/ለውጥ በመደበኛው የትምህርት ዓመት ያለ ESY አገልግሎቶች፣ ተማሪውን/ተማሪዋን ከትምህርት ፕሮግራማቸው የሚገኘውን ጥቅም ሊከለክል ይችላል? ☐ አዎ ☐ አይደለም

የተለየ የህይወት ድጋፍ ክህሎት በደረሰበት የመሻሻል/ለውጥ ደረጃ ትምህርቱ/የESY አገልግሎቶች ቢቋረጡ ተማሪው/ተማሪዋ በመደበኛው የትምህርት ዓመት አንዳንድ የትምህርት ጥቅሞችን እንዳያገኝ/እንዳታገኝ ሊያግደው/ሊያግዳት ይችላል? ☐ አዎ ☐ አይደለም

በIEP ለማሻሻል ዒላማ የተደረጉ ተለይተው የታወቁት ባህርያት ጣልቃ ገብ ሁኔታ ተማሪውን/ተማሪዋን በመደበኛው የትምህርት ዓመት ያለ ESY አገልግሎቶች፥ ከትምህርት ፕሮግራማቸው ከሚያገኘው/ከምታገኘው ጥቅም ይከለክላል? ☐ አዎ ☐ አይደለም

የESY አገልግሎቶች ሳይሰጡ ቢቀር፣ በተማሪው/በተማሪዋ ላይ ያለው ከባድ የስንክልና ተፈጥሮ በመደበኛው የትምህርት ዓመት ከትምህርት ፕሮግራማቸው ከሚገኘው ጥቅም ሊያሳጣው/ት ይችላል? ☐ አዎ ☐ አይደለም

የESY አገልግሎቶች ከተቋረጡ፣ የኔን ተማሪ ከትምህርት ፕሮግራማቸው የሚገኘውን ጥቅም የሚከለክሉ ሌሎች ልዩ ሁኔታዎችስ ይኖራሉ? ☐ አዎ ☐ አይደለም

## የESYን ብቃትና አገልግሎቶች ወይም የህጋዊ ሂደት መብቶቻቸውን በሚመለከት ወላጆች/አሳዳጊዎች ተጨማሪ መረጃ እንዴት ማግኘት ይችላሉ?

በዚህ መጽሔት የተጠቀሱ መረጃዎች ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር በልጃቸው አመታዊ የIEP ስብሰባ ውይይት ይደረግባቸዋል። ህጋዊ ሂደትን የሚመለከት መረጃ በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምርያ ማስታወቂያ መጽሔት/Parental Rights-Maryland Procedural Safeguards Notice የወላጅ መብቶች-የሜሪላንድ ስነ-ስርአት ማስከበርያ ማስታወቂያ ውስጥ ተገልጿል። ወላጆች/አሳዳጊዎች ተጨማሪ መረጃ ወይም የማስታወቂያ መጽሔት ቅጂ ካስፈለጋቸው የሚከተሉትን የMCPS ጽ/ቤቶችን ለመጠየቅ ይችላሉ።


የልዩ ትምህርት ጽ/ቤት
Office of Special Education
301-279-3837

የተራዘመ የትምህርት ዓመት አገልግሎቶች (Extended School Year Services)
301-279-3022

የተማሪ እና የቤተሰብ ድጋፍ እና ተሳትፎ ጽ/ቤት
240-314-4860

# የMCPS የፀረ-መድሎ መግለጫ
# "MCPS NONDISCRIMINATION STATEMENT"

የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS)ዘርን፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ የዘር ሃረግ፣ የብሄር ማንነት፣ ሃይማኖት፣ የስደተኝነት/የፍልሰተኝነት ሁኔታ፣ (ባይሎጂካል/ተፈጥሯዊ) ጾታን፣ (ተለምዷዊ) ስነ-ጾታ፣ የጾታ ማንነት (gender identity)፣ የጾታ አገላለጽ (gender expression)፣ የጾታዊ ግኑኝነት ዝንባሌ/ምርጫ (sexual orientation)፣ የቤተሰብ/የወላጆች (የኑሮ) ደረጃ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ እድሜ፣ ድህነት እና የማህበራዊ ኤኮኖሚያዊ አቋም፣ ቋንቋ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳተኝነት፣ በህገመንግስት ጥበቃ የተደረገላቸውን ገጽታዎች/ባህሪያትን ወይም ተዛማጅነት ያላቸውን (affiliations) መሠረት ያደረገን ሕገ-ወጥ መድሎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት ፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትሕ፣ አብሮነት፣ሁሉን አቀፍነት፣ ለመፍጠርና ለማሳደግ/ለመንከባከብ :- ሲደረግ የቆየ ትጋት ይሸረሽራል/ያበላሻል። የመድልዎ ምሳሌዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡- የጥላቻ ድርጊቶች፣ ሁከት፣ ግዴለሽነት/ደንታቢስነት፣ ጥቃት፣ በጉልበት ማስገደድ፣ ንቀት፣ ወይም ብቀላ። ለተጨማሪ መረጃ፣ እባካችሁ የMontgomery County የትምህርት ቦርድ መመርያ ACA፣ Nondiscrimination, Equity, and Cultural Proficiency/ፀረ-አድልዎ፣ ፍትህ፣ እና ባህላዊ ብቃትን ድህረ እይታ አድርጉበት። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ አሳሳቢ የመሆኑ(ኗ)ን፣ በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ሃቀኛ ወይም የሚታሰብ ግላዊ ጠባዮች የሚተነበዩ አለመሆናቸውን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። መርሁ/ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው ርምጃዎችን የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግ፣ በተቋማት መዋቅሮች ላይ የሚፈጸሙ መሰናክሎች፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል።

| በMCPS ሰራተኛ* ላይ ስለደረሰ መድሎዎ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች ለማቅረብ | በMCPS ተማሪዎች* ላይ ስለደረሰ መድሎዎ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች ለማቅረብ |
|---|---|
| Office of Employee Engagement and Labor Relations<br>Department of Compliance and Investigations<br>850 Hungerford Drive, Room 55<br>Rockville, MD 20850<br>240-314-4899<br>OCOO-EmployeeEngagement@mcpsmd.org | Office of School Administration<br>Office of School Administration Compliance Unit<br>850 Hungerford Drive, Room 162<br>Rockville, MD 20850<br>301-279-3444<br>OSSI-SchoolAdministration@mcpsmd.org |

*ክትትል፣ ቅሬታ/ስሞታ፣ ወይም ስንክልና ላለባቸው ተማሪዎች አመቺ ስፍራ ለመጠየቅ፤ ወደ ልዩ ትምህርት ተቆጣጣሪ ጽ/ቤት፣ የቅሬታ ሰሚና መፍትሔ ሰጪ ን/ክፍል በ ስልክ ቁጥር 301-517-5864 ሊቀርብ/ሊመራ ይችላል። ስለ ሠራተኞች ቦታ፣ ሁኔታ፣ ወይም ማሻሻያ "Inquiries regarding accommodations or modifications for staff" የሚመለከቱ ጥይቄዎች በሠራተኛ ተሳትፎ እና የሥራ ግንኙነት መምሪያ ወደ ቅሬታ ሰሚና ምርመራ ቢሮ ሊመራ ይችላል። 240-314-4899. በተጨማሪ ስለ መድሎ/አድሎአዊነት የቅሬታ ጥቆማ ከዚህ በታች ለተጠቀሱ ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል። the U.S. Equal Employment Opportunity Commission, Baltimore Field Office, City Crescent Bldg., 10 S. Howard Street, Third Floor, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights, Lyndon Baines Johnson Dept. of Education Bldg., 400 Maryland Avenue, SW, Washington, DC 20202-1100, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህን ሰነድ ከእንግሊዝኛ በተጨማሪ በሌሎች ቋንቋዎች አማራጭ የውሂብ/ሕትመት ቅርጽ ያለውን በአካል ጉዳተኝነት የሚኖሩ አሜሪካኖች ህግ በሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች - የሕዝብ ማስታወቂያ ጽ/ቤት በስልክ ቁጥር፡- 301-279-3853፤ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.org. በጥየቃ ለማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚፈልጉ ወይም በምልክት የተዘጋጀ ትርጉም ለሚያስፈልጋቸው፤ የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶችን MCPS የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን Office of Interpreting Services በስልክ ቁጥር፡- 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) ወይም Interpreting_Services@mcpsmd.org.መጠየቅ ። የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS)፤ ወጣት ስካውቶችን (ወንድ/ሴት) እና ለሌሎችም የሚመለከታቸውን ወጣት ቡድኖችን በእኩል ያስተናግዳቸዋል።

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
ROCKVILLE, MARYLAND

ህትመት፡- የልዩ ትምህርት ፅ/ቤት የቁሳቁሶች አስተዳደር መምርያ
Department of Materials Management for the Office of Special Education
ትርጉም፡- የቋንቋዎች ትርጉም አገልግሎት ክፍል
Language Assistance Services Unit • Department of Communications

0450.18 • Editorial, Graphics & Publishing Services • 10/17 • NP